# የሰለጠነ ማሕበረሰብ ከሚጠይቀው የበዛም ያነሰም አንጠይቅም

በአለማየሁ ገብረማርያም(ፕሮፌሰር)

ፕሬዚዳንት ኦባማ በቅርቡ ለቱርክ ሕግ አውጭዎች አንድ ታሪካዊ ንግግር አድርገዉላቸዋል፤ ነገር ግን ይህ ንግግራቸው ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለውና እስከ አሁን ይፋ ስላልተደረገው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያቸው ጠቃሚ ፍንጭ የሰጠ ነው፡፡ ኦባማ ለዓለም ሰላም እየወሰዱ ያሉት እርምጃዎች ለአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ በጣም አስፈላጊውን ጤንነት ብቻም ሳይሆን የሚመልሰው አሜሪካ ከተቀረው ዓለም ጋር ለሚኖራት መጪ ግንኙነቶች ድጋፍ የሚሰጥ አዲስ ምሰሶ የሚያቆም ነው፡፡ ይህም ማለት፤የአሜሪካንን ዴሞክራሲያዊ እሳቤዎች ማክበር፣ የእስልምና እምነት ተከታዮችን ከነእምነታቸው ማክበር፣ሰብአዊ መብቶችንና የሕግ የበላይነትን ማክበር፣በወዳጃሞች መካከል እርስ በእርስ ለጋራ ጥቅም መከባበር እና ከተጠቀሱት ነጥቦችም በላይ ከጠላት ጋር በመከባበር ላለመግባባት መግባባት፡፡

ንግግሩ የኦባማን ትክክለኛ ብቃት ቁልጭ አድርጎ ያሳየ ነበር - ተዓማኒ፣ ሰቃኘ፣ በተምሳሌታዊ አገላለጽ፣ ተስፋና ቃል የታጨቀበት፤ እና በተለይ ለዴሞክራሲ፣ለነፃነትና ለሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች አነቃቂ ነበር፡፡ በጥቅሉ የዩ.ኤስ. አሜሪካንን የውጭ ፓሊሲ ኡደትን ፕሬዚዳንቱ በምስል ያስቀመጡ ሲሆን የወቅቱን ዓለም አቀፍ ፈተናዎችና የሰው ልጅ አማራጮችን በአንፀባራቂ ቃላት አስቀምጠዋል፡- «በመጭዎቹ ዓመታት የምንከተላቸው አማራጮች መጭው ጊዜ በፍርሀት ወይስ በነፃነት፤በድህነት ወይስ በብልጽግና፤በብጥብጥ ወይስ በፍትሕ፤ እና ደህንነቱ በተጠበቀና በዘላቂ ሰላም መቀረጽ አለመቀረፁን የሚወስኑ ናቸው፡፡»

ፕሬዚደንቱ እንዳሉት ቱርኮች ትክክለኛ ምርጫዎችን አድርገዋል ምክንያቱም «አስቸጋሪ የፖለቲካ ማሻሻያዎችን በመተግበራቸው» በውጤቱም «የመንግስት-ደህንነት ፍ/ቤቶችን ለመደመሰስ፣ጠበቃ የማግኘት መብት ለሁሉም ለማዳረስ፣የወንጀለኛ መቅጫ ሕግን ለማሻሻልና የፕሬስና የመደራጀት ነፃነትን ለማጠናከር» ችለዋል፡፡ ለውጣቸውም ቀጣይነት ኖሮት እንዲዘልቅ ኦባማ አጥብቀው ጠይቀዋል፤ «ዴሞክራሲ በቆመበት ለመርገጥ አይቻለውምና - ወደፊት መገስገስ ግድ ይላቸዋል፡፡ የሐይማኖትና ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ወደ ጠንካራና ለውጥ አድራጊ ሲቪል ማህበረሰብ ይመራሉ . . . ለሕግ የበላይነት የማይናወጥ ቁርጠኝነት መኖሩ ለሁሉም ዜጋ የሚዳረስ ፍትሕን ለማስገኘት የሚያስችለውን ደህንነት ለማምጣት የሚያስችል ብቸኛው መንገድ ነው፡፡»

ኦባማ ሰብዓዊ መብቶችን አስመልክተው አቋማቸውን ከዚህ (ንግግራቸው) አስበልጠው ግልጽ ሊያደርጉት አይቻላቸውም፡፡ ፕሬዚደንቱ ለሰብዓዊ መብት ጥሰቶች አመክንዮ እንደሌለ ገልፀዋል፡፡ «ማሰቃየት፣ ተከሳሾች መሰረታዊና ሕጋዊ (ሕገመንግስታዊ) መብቶቻቸውን መንፈግ ወይም ዓለም አቀፍ ሕግንና የሰብዓዊ

መብቶች ኮንቬንሽኖችን የሚጥሱ ፍትሀዊነት የሌላቸው እርምጃዎች ፀረ-አሜሪካ» መሆናቸውን ፕሬዚዳንቱ አውጀዋል፡፡ «የራሳችንን ዴሞክራሲያዊ መሰረቶች ከተገበርናቸው የተጋፈጥነውን እያንዳንዱን ፈተና በድል መውጣት ይቻለናል፡፡ ስራው በጭራሽ አልተጠናቀቀም፡፡ ለዚህም ነው በዩ.ኤስ. አሜሪካ በቅርቡ ጓንታናሞ «ማጎሪያ» ካምፕ እንዲዘጋ ትዕዛዝ የሰጠነው እና ካለአንዳች ልዩ ድንጋጌ ወይም «በቀር» ወይም አውዛጋቢ አገላለጽ ምንም አይነት የማሰቃየት ተግባር እንዳይፈፀም የከለከልነው፡፡» ፕሬዚደንቱ የአሜሪካንን የባሪያ ንግድና የተፈፀሙ ኢፍትሀዊነት ውርሶችን በንግግራቸው በግልጽ አንስተዋል፤ «ዩናይትድ ስቴትስ የራሳችንን የተወሰኑ ጨለማ ወቅቶች (ለማደብዘዝ) አሁንም እየሰራች ነው፡፡ . . . እናም አገራችን በነባር አሜሪካውያን አያያዝ (እና የባሪያ ንግድ) ያለፈ የታሪክ ውርሷ ምክንያት አሁንም እየታገለች ነው፡፡» ኦባማ በፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ቅስቀሳቸው ወቅት የዘር ማጥፋት (ወንጀሎችን) አበክረው እንደሚያወግዙ ቃላቸውን ሰጥተው ነበር፤ «የአርመንያውያን የዘር ጨፍጨፋ ውንጀላ፣የግል አስተያየት ወይም አመለካከት አይደለም፤በበርካታ ታሪካዊ ማስረጃዎች ተጠርዞ ያለ እውነታ ነው፡፡ አሜሪካ የአርመንያውያን የዘር ጭፍጨፋ አስመልክቶ እውነቱን የሚናገርና ሁሉንም የዘር ጭፍጨፋዎችን በሀይል የሚመልስ መሪ ይገባታል፡፡ እናም ያን ሰው ለመሆን አቅጃለሁ፡፡

ኦባማ ለመጭው ጊዜ ያነገቡት ራዕይ - ህልሙ - የተመሰረተው ለሰብዓዊ ፍጡር ቅድሚያ በመስጠት ላይ ነው፤ «በርካታ ህፃናት ለሰኬታቸው የሚያስፈልጋቸውን ትምህርት እንዲያገኙ ለመርዳት እንፈልጋለን፡፡ ሕዝብ (ለበሽታ) ተጋላጭ በሆነባቸው አካባቢዎች የጤና ጥበቃ እንዲስፋፋ እንፈልጋለን፡፡ ለጠቅላላ ሕዝብ ብልፅግናን ለማምጣት በሚያስችሉ የንግድና የኢንቨስትመንት (ዘርፎችን) ለማስፋፋት እንፈልጋለን፡፡» ፕሬዚዳንቱ፣ «በመጭዎቹ ወራት ግቦቹን ወደ ተግባር ለመለወጥ ተለይተው የተቀመጡ ፕሮግራሞችን አቀርባለሁ፡፡ አትኩሮታችን የሚሆነው በጠቅላላ ከሙስሊሙ ዓለም ሰዎች ጋር በመተባበር የጋራ ተስፋችንና ህልማችንን ተግባራዊ ለማድረግ ምን ማድረግ እንችላለን በሚለው ላይ ነው፡፡ እናም (ወደ ፊት) ይህን ወቅት ሕዝብ ወደኋላ ተመልሶ በሚመለከትበት ጊዜ ዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ የወዳጅነት እጇን (እኮ) ዘርግታልን ነበር ይባል፡፡» በማለት በንግግራቸው ተናግረዋል

... አሜሪካ ለነፃነት፣ለዴሞክራሲና ለሰብዓዊ መብቶች እሳቤዎች ተቆርቋሪ ነች! ኦባማ «አሜሪካ የትና ምንን በተመለከተ እንደምትቆረቆር» በሚናገሩበት ወቅት የአሜሪካ የዴሞክራሲ፣የነፃነትና የሰብዓዊ መብቶች እሳቤዎች በአላስፈላጊና ስልጣን ሳይኖራቸው እንደላቸው በሚንቀሳቀሱ አምባገነኖች እና እዚህ ግቡ በማይባሉ ደም በጠማቸው ወንበዴዎች አደጋ በተጋረጠባት ዓለማችን ውስጥ የተጠቀሱት እሳቤዎች የአሜሪካንን የውጭ ፖሊሲ እንደሚመሩ ለመግለፅ ነው፡፡ «ከእኛ ጋር ካልሆንክ የእኛ ጠላት ነህ፤

ከእኛ ጋር ከሆንክ - እጅህ በደም ቢለወስም እንኳን - ወዳጃችን ነህ» የተባለባቸው ወቅቶች አሁን አልፈዋል:: የኦባማ መልዕክት:- «የወዳጅነት እጃችንን እንዘረጋልሀለን፤ ሆኖም እጅህን ያጨማለቀውን ደም ለመሸሸግ ብለህ መዳፍህን የምትጨምቅ ከሆነ ግን የአማሪካ ወዳጅ አይደለህም::» የሚል ነው:: በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች አብዬት አሜሪካ በአመራርነት ግንባር ቀደምና ማዕከል እንድትሆን የኦባማ ፍላጎት ነው:: (አላማውም ከተሳካ) በመላው ዓለም ለዴሞክራሲ፣ለነፃነትና ለሰብዓዊ መብቶች (መከበር) አዲስ ቀን - አዲስ ዘመን - እንዳሚሆን ቃል ገብቷል::

ማሰቃየት፣የተከሳሽን ሕገመንግስታዊ መብቱን በኢፍትሀዊ አካሄድ መንፈግ አግባብ እንዳልሆነና የኋላ ታሪክን በማስታወስ በነባር አሜሪካውያንና በባሪያዎች ላይ የተፈፀመውን ኢፍትሃዊነት የተቸው ፕሬዚዳንት፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የዴሞክራሲ ደረጃና ሁኔታ ለመደገፍ የወዳጅነት እጁን ይዘረጋል? ... ጓንታናሞ ካምፕና የሲ.አይ.ኤ «የደህንነት» እስር ቤቶች እንዲዘጉ ትዕዛዝ ያስተላለፈው ፕሬዚዳንት (የአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት በ2008 «አስከፊ፣ለህይወት አደገኛና የተጨናነቀ» ብሎ የገለፀውን) በመቶዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች የሚገኙባቸውን «እስር ቤቶች» እንዳሉ እንዲቀጥሉ አሜሪካውያን ጥረው ግረው ካገኙት ገቢ በግብር መልክ ለመንግስታቸው ከሚሰጡት ገንዘብ ተወስዶ ለኢትዮጵያ በመለገስ ይቀጥላሉ? ለዴሞክራሲያዊ ለውጥ የመንግስት-ደህንነት ፍ/ቤቶች መደመሰስን፣ ጠበቃ የማግኘት መብት ለሁሉም ማዳረስን፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግን ማሻሻልንና የፕሬስና የመደራጀት ነፃነትን ማጠናከር መስፈርት አድርገው የተጠቀሙት ኦባማ መያዶችን ወንጀለኛ ካደረገ፣ ካሰረና ጋዜጠኞችን ካሳደደ ጋር ይቆራኛሉ? የቀድሞ የሲቪል መብቶች ጠበቃና ሕገመንግስታዊ ምሁር - ለሕግ የበላይነት የማይናወጥ ጽናት እንዳላቸው ያወጁ - ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ ሥርዓትን አቅፈው ይይዛሉ? ምላሹን አስመልክተን እንዲህ እንላለን - «እንዴት ተደርጎ!»

የሕግ የበላይነትና የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ ለአሜሪካ፣ለቱርክና ለተቀረው ዓለም መልካም ከሆኑ ለኢትዮጵያም መልካም ናቸው እንላለን:: ማንኛውም የሰለጠነ ማሕበረሰብ እንዲኖረው ከሚጠይቀው የበለጠም ሆነ ያነሰ ምንም አንጠይቅም፤በሕዝብ ፍቃደኝነት የተመረጠ መንግስት (እና ምርጫ ያልተሰረቀበት)፤ ሰብዓዊ መብቶችንና ሲቪል ነፃነቶችን ጠብቆ የሚገዛ መንግስት፤ ለሁሉም መንግስታዊ ተግባሮቹና መፈፀም ሲገባው ላልፈፀማቸው ለሕብብ ተጠያቂ መንግስት፤ ከሙስና የፀዳና የሕዝብ ንብረትን ከመጭበርበር እና ብክነት በቀናኢነት የሚጠብቅ መንግስት፤የጎረቤቶቹን ሉአላዊነት የሚያከብር መንግስት፤ በሕግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ ማንም ሕግን ለፖለቲካ ወይም ለግል ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ ለመጠቀም የሚያስችለው መብት ወይም እድል የማያገኝበት ማሕበረሰብ፤ፍ/ቤቶች ፍትሕን እንጂ በሙስና የተዘፈቁ ባለስልጣናትን ጥቅም

ለማስጠበቅ የማይሰሩበት ማሕበረሰብ፤የሚታወቁና ተጠርጣሪ የሰብዓዊ መብቶች ጣሾችን፣ በሰብአዊ ፍጡር ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የሚፈፅሙትን እና ንፁህ ግለሰቦችን፣የተቃዋሚ መሪዎችን፣እና ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ ሥርዓትን በመቃወማቸው ለአመታት ታስረው ያሉ የፖለቲካ እስረኞችን ነፃ ለማውጣት የማይፈነቅለው ድንጋይ የሌለው የፍትሕ ሥርዓት በኢትዮጵያ እንዲኖር እንጠይቃለን፡፡

ፕሬዚዳንት ኦባማ በንግግራቸው ቆየት ያለ የቱርክ አባባል ተጠቅመዋል፤ «እሳትን በነበልባል ማጥፋት አይቻልም፡፡» እርግጥ ነው ፕሬዚዳንቱ እሳትን ማጥፋት የሚቻለው «ፍትሕን እንደ ውሀ እንዲፈስ እና ፅድቅናን እንደ ኸረት እንዲወርድ» ሲደረግ ብቻ እንደሆነ አሳምረው በደንብ ያውቁታል፡፡ ቤትህ በእሳት የተያያዘ ለታ እሳቱን ለማጥፋት ነበልባል አያሻህም፡፡ እሳት አጥፊዎች ናቸው የሚያስፈልጉህ፡፡» ኢትዮጵያም ውስጥ ጠንካራ ወንድና ሴት እሳት አጥፊዎች ያስፈልጉናል፡፡

/አለማየሁ ገብረማሪያም በካሊፎርኒያ ስቴት ዩኒቨርስቲ፣ ሳን በርናንዲኖ የፖለቲካል ሳይንስ ፕሮፌሰር ሲሆኑ ሎስ አንጀለስ በሚገኝ ተቋም የህግ ኮንሰልታንት ናቸው/